# *የህዳሴዉ ሌቦች*

*“የታጠቅ ጎራዴ ብረት የነበረ እየቀላ ሄደ ቱርክ እየመሰለ” - አዎ ቱርክ እየመሰለ! የአፄ ቴዎድሮስን የመጨረሻ አመታት በተለይ እቴጌ ተዋበች ከሞቱ በኋላ አፄዉ ያሳዩት የነበረዉን ጭካኔ ለመግለጽ የተቀኘ ቅኔ ነዉ። የዛሬዉ ጉዳዬ ከአፄ ቴዎድሮስ ጭካኔ ጋር አይደለም። የዛሬዉ ጉዳዬ በጭካኔ፤ በጥላቻ፤ በክህደትና በዝርፍያ ተወዳዳሪ ከሌላቸዉ ከመለስ ዜናዊና ከጓደኞቹ ጋር ነዉ። መይሳዉ ቢጨክንም አገሩን ይወዳል ለዚህ ነዉ የንግስት ቪክቶሪያ ግሳንግስ እጄን ከሚይዘዉ ብሎ ሽጉጡን የጠጣዉ። አፄ ቴዎድሮስ እንደዚያ ቤ/ክርስትያንና ተከታዮቿ፤አድመዉባቸዉ፤ የአገር ዉስጥ ስልጣን ተሻሚዎች እያሳደዷቸዉና ከዉጭ ደግም እንግሊዝን በመሰለ መሠሪ ኃይል ተከብብዉ በነበሩበት ግዜ የሳቸዉ ትልቁ ዕዳ የኢትዮጵያ እድገትና አንድነት እንጂ የቪክቶሪያን ገጸ በረከት ወይም የአገር ቤቱን ወርቅና ብር ማግበስበስ አልነበረም። ለዚህ ነዉ ይህ አለግዜዉ የተፈጠረ ጀግና ሰዉ እስከወዲያኛዉ ከፍለን መጨረስ የማንችለዉን ዕዳ ከፍሎልን “አንቺ እማማ” እንዳለ የተሰናበተን።*

*ስማ አንተ አንባቢ አይዞህ፤ ተረጋጋ፤አይንህን አብራ ልብህን ክፈት ዛሬ ብዙ የምልህ አለኝ። መግቢያዬ ላይ “ቱርክ” ብዬ የጀመሩኩት አለምክንያት አይደለም። ከሰሞኑ መለስ ዜናዊና ኃይለማሪያም ደሳለኝ ወደ አንጋፋዋ የቱርክ ከተማ ወደ ኢስታንቡል ተጉዘዉ ነበር። ጉደዩ እንደዚህ ነዉ - የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በዕድገት ወደ ኋላ ለቀሩ አገሮች ያዘጋጀዉ 4ኛዉ መደበኛ ስብሰባ ኢስኢታንቡል ዉስጥ ይካሄድ ነበር፤ የስብሰባዉ አቢይ ርእስ “ኋላ ቀር አገሮች እንዴት ከድህነትን ከኋላ ቀርነት ተላቀቀዉ ከመካከለኛ ገቢ አገሮች ተረታ ይሰለፋሉ” የሚል ነበር። እንግዲህ ይታያችሁ እዚህ ስብሰባ ላይ ለመገኘት ነዉ መለስ ዜናዊና ከሰሞኑ የተከራየዉ አዲስ መኪናዉ ሃይለማሪያም ደሳለኝ አገር ጤና ነዉ ብለዉ ኢስታንቡል የተጓዙት። የሚገርመዉ ስብሰባዉ ተጀምሮ እስኪጨረስ ድረስ ለወትሮዉ ወይም አዲስ አበባ ዉስጥ ባዋቂነታቸዉ የሚደነቁት አቶ መለስ ዜናዊና ታማኝ ሎሌዉ አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ የእስታንቡሉ ስብሰባ ላይ መኖራቸዉ የታወቀዉ ስብሰባዉ ተጠናቅቆ ከአዳራሹ ሲወጡ ብቻ ነበር። ስብሳባዉ ይካሄድ በነበረበት ግዜ እነዚህ ላለፉት አምስት አመታት የኢትዮኢጵያ ኤኮኖሚ በድርብ አህዝ አደገ እያሉ ጆሯችንን ያሰለቹት ዋሾ ቁጥር አንድና ዋሾ ቁጥር ሁለት ግምባራቸዉ ከጠረቤዛዉ ጋር የተጣበቀ እስኪመስል ድረስ በሀፍረት አጎንብሰዉ ነበር።*

*በእንግዲህ ልብ በሉ- እነዚህ ጥፋታቸዉ በተነገራቸዉ ቁጥር ተናጋሪዉን መዝለፍ፤ማዉገዝና ማሰር የለመዱ ካለኛ አዋቂ የለም ባዮችና ነዉረኞች ናቸዉ አገራችንን ወክለዉ ኢስታንቡል የተጓዙት፤ ደስ የሚለዉ ግን እነዚሁ ተመፃዳቂዎች ናቸዉ በኢስታንቡሉ የተ. መ. ድ መድረክ ላይ “ሌቦች” የተባሉት። የሌባ ማጎንበስ እኔን ብዙም አያስገርመኝም- ድሮም ቢሆን ሰዉ የሚዘልፈዉና የሚደበቀዉ እፍረቱን እንደ መስታወት ከሚያሳየዉ ሰዉ ነዉ፤ ችግሩ መለስ ዜናዊና መኪናዉ ሃይለማሪያም ደሳለኝ ጉዳቸዉ ፊታቸዉ ላይ ሲነገር እንደልማዳቸዉ እንዳይዛለፉ ቁጭ ያሉት የተ.መ. ድ ስብሰባ ላይ ነዉ እንጂ እዚያ የለመዱት ፓርላማ ዉስጥ አይደለም፤ እንዳይሸሹ ደግሞ ባህር አቋርጠዉ የሄዱት የክብር ጥሪ ተደርጎላቸዉ ነዉ። እዚህ አጣብቂኝ ዉስጥ ገብተዉ ነዉ የህዳሴ ግድብ እንገነባለን ባዮቹ አቶ መለስና አቶ ሃይለ ማሪያም የ”ህዳሴዉ ሌቦች” የመሆናቸዉ ዜና ይፋ የወጣዉ።*

*የኢትዮጵያ ህዝብ ሀብቴን፤ ንብረቴንና የታሪክ ቅርሴን ታይቶ በማይታወቅ መልኩ እየተዘረፍኩ ነዉ ብሎ መጮህ ከጀመረ ቆይቷል። ወያኔ ደግሞ በበኩሉ ይህንን መጠነ ብዙ ዘረፋዉን አጋልጠዉ የፃፉ የአገር ዉስጥ ጋዜጠኞችን ዘብጢያ ወርዉሯል፤ የዉጭ አገር ጋዜጠኞችን ኢትዮጵያ እንዳይገቡ ከልክሏቸዋል-*

ድህረ ገጾችን፤ሬዲዮ ጣቢያዎችንና ቴሌቪዥን ጣቢያዎችን አፍኖ አፋቸዉን ዘግቷል። ባጠቃላይ የወያኔ የአፈና ኃይል እዉነትን ደብቆ ለማቆየት ብዙ ጥረት አድርጓል። የኢስታንቡሉ ጉባኤ ግን ጠ/ሚኒስትርና ምክትል ጠ/ሚኒስትር ተብዬዎቹን ሁለቱን የስርአቱን ቁንጮዎች በእማኝነት አስቀምጦ ነዉ የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣኖች በስሙ ከሚለምኑት ደሃ ህዝብ ላይ 8.4 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር መስረቃቸዉን ይፋ ያወጣዉ። አዎ! የምነግራችሁ ወይም የማወራችሁ ተረትም ምትሀትም አይደለም፤ ወይም እንደቀድሞዉ እሱ አለዉ እሷ አለችዉ ተብሎ የሚታለፍ ተራ ጉዳይም አይደለም። ሁለቱን ከፍተኛ የወያኔ ሹሞች ፊት ለፊቱ አስቀምጦ ደሃዉን የኢትዮጵያ ህዝብ ከ140 ቢሊዮን ብር በላይ ዘርፋችሁ ባህር ማዶ ባንኮች ዉስጥ ከምራችኋል ብሎ የተናገረዉ በተአማኒነቱ ማንም የማይጠራጠረዉ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ነዉ።

መለስ ዜናዊንና ሎሌዉን ኃ/ማሪያም ደሳለኝን ያሳፈረዉን ሪፖርት (እፍረት የሚሰማቸዉ ከሆነ) በንባብ ያሰሙት የተ. መ. ድ የልማት መርሃ ግብር ዋና ሐላፊ ወ/ሮ ሄለን ክላርክ በመግቢያ ንግግራቸዉ እንደዚህ ነበር ያሉት - በህገ ወጥ መንገድ ከታዳጊ አገሮች እየወጣ ኃብታም አገሮች ዉስጥ የሚከማቸዉ ገንዘብ የታዳጊ አገሮችን የኤኮኖሚና ማህበራዊ እድገት በእጅጉ ይጎትታል፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ድህነትንና ኋላ ቀርነትን ይቀንሳል ተብሎ በተ.መ.ድ አቀነባባሪነት በተጀመረዉ የሚለኒየሙ የእድገት ግቦች አፈጻጸም ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያደርጋል። ወ/ሮ ሄለን ከዚህ በተጨማሪ ታዳጊ አገሮች በጥቅሉ በየአመቱ እስከ አንድ ትሪሊዮን ዶላር ድረስ በሙሰኝነት እንደሚያጡ ገልፀዉ ይህ ገንዘብ በየአገሩ ለልማት ስራ ቢዉል ኖሮ እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉን ት/ቤቶች፤ ኮሎጆች፤ ዩኒቨርሲቲዎች፤ ሆስፒታሎች፤ የንጹህ ዉኃ አገልግሎቶች፤ የመገናኛ አዉታሮች፤ የትራንስፖርት መሰረተ ልማቶችና የእርሻና የእንዱስትሪ ተቋማትን መገንባትት ይችል ነበር። የወይዘሮ ሄለን ሪፖርት የተጠቃለለዉ - ገንዘብ ወደ ዉጭ ከሚያሸሹ ደሃ አገሮች ዉስጥ ኢትዮጵያ በአፍሪካ 4ኛ በአለም 9ኛዋ አገር መሆንዋ ከተነገረ በኋላ ነዉ። አንባቢ ሆይ እንግዲህ አስተዉል፤ እነ መለስ ዜናዊ “ድርብ አሀዝ” እድገት ብለዉ የሚጠሩት ይህንን ነዉ። የሚገርመዉ በአለም ደረጃ እድገታችን ሲለካ የአለም ጭራ ሌብነታችን ሲለካ ደግሞ የአለም አዉራ ሆነናል።

ለመሆኑ እንዴት አድርገዉ ነዉ እነዚህ ምሽላቆች እንደዚህ ለምድርም ለሰማይም የከበደ መጠነ ሰፊ ገንዘብ መስርቅ የቻሉት? እዚህ ላይ አንድ መገንዘብ ያለብን ሃቅ አለ፤ እሱም በአንድ በኩል ይህ የተ. መ. ድ ይፋ ያወጣዉ 8.4 ቢሊዮን ዶላር ለግዜዉ በመረጃ ተደግፎ የተደረሰበት ነዉ እንጂ ወያኔዎች በልጆቻቸዉና በቅርብና ሩቅ ዘመዶቻቸዉ አማካይነት ከአገር ያሸሹት የህዝብ ኃብትማ ዬትዬለሌ ነዉ - በሌላ በኩል ደግሞ ጥናታዊ ሪፖርቱ የሚያጠቃልለዉ እንደ አዉሮፓ አቆጣጠር ከ1991- 2008 ያለዉን ግዜ ብቻ ነዉ። እንግዲህ ይታያችሁ ወያኔዎች የዘረፉት እያንዳንዱ ገንዘብ በጥናት የሚደረስበት ቢሆንና ከ2008 እስከ 2011 ያሉትን ሦስት አመታት ቢያጠቃልል እኛ ኢትዮጵያዉያን የተዘረፍነዉ ገንዘብ ብዛቱ ከ20 ቢሊዮን ዶላር ቢበዛ እንጂ አያንስም፡ ሃያ ቢሊዮን ዶላር ደግሞ የኢትዮጵያ የአምስት አመት በጀት ነዉ።

በኢስታንቡሉ ጉባኤ ላይ የተ. መ . ድ ሪፖርት በግልፅ እንዳስቀመጠዉ የደሃ አገሮች መሪዎች ገንዘብ ከአገራቸዉ እየሰረቁ የሚያስወጡት በሚከተሉት ሁለት ዋና ዋና መንገዶች ነዉ፡ 1) 65% የሚሆነዉ ገንዘብ ከደሃ አገሮች በህገ ወጥ መንገድ እየወጣ ወደ ኃብታም አገሮች የሚጎርፈዉ የሸቀጦችን ዋጋ በማዛባት ወይም ፈረንጆቹ “Trade Mispricing” እያሉ በሚጠሩት እጅግ በረቀቀ የሌብነት ዘዴ ነዉ . . . ጉዳዩ እንደዚህ ነዉ - በሁለት አገሮች መካከል የሸቀጥ ልዉዉጥ ሲካሄድ (import & export)

ሸቀጡ የተገዛበት ደረሰኝ በቀጥታ ወደ አስመጪዉ አገር መሄድ ሲገባዉ ወደ ሌላ በሸቀጥ ልዉዉጡ ዉስጥ ወደሌለበት ሦስተኛ አገር እንዲሄድ ይደረጋል። ይህ ሦስተኛ አገር ደግሞ እጅግ በጣም ዝቅተኛ የታክስ ስርአት ያለበትና ሆን ተብሎ የሚመረጥ አገር ነዉ። እዚህ ሦስተኛ አገር ዉስጥ ደረሰኙ ላይ ያለዉ ዋጋ ለአስመጪዉ ነጋዴ በሚያመች መልኩ ይቀየርና ወደ ዕቃ አስመጪዉ አገር ይላካል። ይህ አይነቱ አሰራር ዕቃ አስመጪዎችም ሆኑ ላኪዎች የሚጠቀሙበት አሰራር ስለሆነ አንድ አገር ከኢምፖርትና ኤክስፖርት ዘርፎች ማግኘት የሚገባዉን ብሔራዊ ገቢ እጅግ በጣም አናሳ ያደርገዋል ወይም ወደ መንግስት ካዝና መግባት ያለበት የህዝብ ገንዘብ ግለሰቦች ኪስ ዉስጥ ያስቀረዋል።

ኢትዮጵያ ዉስጥ ዋና ዋናዎቹ ዕቃ ላኪዎችና አስመጪዎች በግልም ሆነ በድርጅት የህወሀት አባላት ብቻ ናቸዉ። ድርጅትን በተመለከተ በተለይ የትግራይ ተራድኦ [EFFORT] በመባል የሚታወቀዉና በየክልሉ ተተክሎ የህዝብን ንብረት የሚዘርፈዉ ድርጅት ኢትዮጵያ ወስጥ የሚካሄደዉን አይን ያወጣ ዝርፍያ የሚያቀነባብርና የሚያመቻች ዋነኛ የህዝብ ጠላት የሆነ ተቋም ነዉ።

2) ሁለተኛዉ ወያኔዎች የኢትዮጵያን ህዝብ የሚዘርፉበት መንገድ ሙሰኝነት ሲሆን እሱም ከዉጭ አገር ጨረታ አሸናፊዎች ጉቦ መቀበልን፤ የዉጭ ምንዛሪ ማምታታትን፤ ከመሬት ሽያጭና ኪራይ የሚገኝን ገቢ ኪስ ዉስጥ መክተትንና የህዝብ ንብረትን ለግል ባለኃብቶች በመስጠት የሚገኙ ጥቅማጥቅሞችን ያጠቃልላል። (ለምሳሌ የአዶላ? ወርቅ ማዕድን በርካሽ ለአላሙዲን ተሰጥቷል). ባጠቃላይ ሙሰኝነት የወያኔ አባለትና ምስለኔዎቻቸዉ ከላይ እስከታች የተሰማሩበትና የህዝብን ንብረት በቀጥታ የሚዘርፉበት መንገድ ነዉ።

ከላይ እንደተጠቀሰዉ መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ ከደሃዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የዘረፉት ገንዘብ መጠኑ 8.4 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወይም 140.28 ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር ነዉ። ይህ ገንዘብ እንኳን ያለ እርዳታ ዉላ ማደር ለማትችለዉ ኢትዮጵያ ለእርዳታ ሰጪዎቹም አገሮች ቢሆን እጅግ በጣም ብዙ ገንዘብ ነዉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ እንግዲህ ልብ በል - እነ መለስ ዜናዊ ይህን ያክል መጠን ብዙ ገንዘብ ዘርፈዉ ከአገር እያሸሹ ነዉ አንተን አንዴ ገንዘብ አዋጣ፤ ቦንድ ግዛ ወይም ደሞዝህን አምጣ እያሉ የሚያስጨንቁህ። የሚገርመዉ የህዳሴዉን ግድብ በተመለከተ ከህዝብ የተሰበሰበዉን ገንዘብ እንዲቆጣጠሩ የህዝብ አካል ተብለዉ አደራ የተሰጣቸዉ እነ በረከት ስምኦን በዘረፋና አይን ባወጣ ቅሚያ ቀዳሚዉን ቦታ የያዙ ሰዎች ናቸዉ። ከዚህ በተጨማሪ እነመለስ ዜናዊ ቦንድ ግዛ እያሉ ህፃንና ሽማግሌ ሳይለዩ ሁሉንም የሚጨቀጭቁት አንድ ግድብ ለመስራት ነዉ፤ ለመሆኑ እነሱ ከህዝብ ዘርፈዉ ባህር ማዶ የላኩት ገንዘብ ወደ አገር ቤት ቢመለስ ምን መስራት ይቻላል? ለመልሱ የሚከተለዉን ሰንጠረዥ ይመልከቱ።

ሠንጠረዡ ላይ የተቀመጡትን ቁጥሮች አንባቢዉ በጥንቃቄ ሊመለከታቸዉ ይገባል። አንዳንዶቹ ቁጥሮች ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚታየዉን ሁኔታ ላያመለክቱ ይችላሉ፤ ለምሳሌ ሠንጠረዡ ላይ አንድ ዩኒቨርሲቲ 30 ሚሊዮን ዶላር ፤አንድ መለስተኛ ኮሌጅ ደግሞ 15 ሚሊዮን ዶላር ተገምተዋል። ይህ ግምት የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ቁጥር ለማብዛት ብቻ በየቦታዉ እንደ ችካል የሚተክላቸዉን ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆችን አይመለከትም። 30 ሚሊዮን ዶላር መለስ ዜናዊ በየቦታዉ የሚተክለቸዉን አይነት 10 ዩኒቨርሲቲዎች መስራት ይችላል። በዚህ ጽሁፍ መሠረት ዩኒቨርሲቲ ሲባል በስነ ስርአት ብዙ ነገሮችን ያሟላ ዘመናዊ የመማሪያ ተቋም ማለት ነዉ።

*በዚህ ጽሁፍ ዉስጥ ከዚህ በታች የተቀመጠዉን ሰንጠረዥ የተጠቀምኩት ኢትዮጵያን ለመሰለ ደሃ አገር 8.4 ሚሊዮን ዶላር ምን ያክል ብዙ ገንዘብ እንደሆነ ፍንጭ ለመስጠት ነዉ እንጂ በስነ ስርአት እያንዳንዷን ዶላር ለአገር ጥቅም ብቻ የሚያዉል መንግስት ቢኖረን ኖሮ 8.4 ቢሊዮን ዶላር ሠንጠረዡ ላይ የሚታየዉን እጥፍ ስራ ሊሰራ ይችላል። እዚህ ላይ አንባቢዉ ማስተዋል ያለበት ነገር ቢኖር 8.4 ቢሊዮን ዶላር ከህዝብ ላይ የዘረፈዉ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሰንጠረዡ ላይ ከተዘረዘሩት የልማት ፕሮጀክቶች ዉስጥ የአባይን ድልድይ ብቻ ለመስራት ነዉ ሠራተኛዉን ደሞዝህን፤ ነጋዴዉን ትርፍህን ተማሪዉን ደግሞ ከምትበላዉ ቀንሰህ አምጣ እያለ ህዝብን የሚያሰቃየዉ! የሚገርመዉ ወያኔዎች እስከዛሬ የዘረፉት በቅቷቸዉ ዝርፍያቸዉን ቢያቆሙ ብቻ ረሃብና ችግር ከአገራችን የሚወገዱበት ግዜ ሩቅ አይሆንም።*

| **የሚሰሩ ሥራዎች** | **ለእያንዳንዱ ስራ የሚወጣ ወጪ** | **ብዛት** | **ጠቅላላ ወጪ** | **የክልል ድርሻ** |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | $150,000 | 90 | $ 13,500,000.00 | 9 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት / ክልል |
| ዩኒቨርሲቲ | $30,000,000 | 18 | $ 540,000,000.00 | 18 ሁኒቨርሲቲ / ክልል |
| መለስተኛ ኮሌጅ | $15,000,000 | 27 | $ 405,000,000.00 | 27 መለስተኛ ኮሌጅ / ክልል |
| ሆስፒታል | $35,000,000 | 36 | $ 1,260,000,000.00 | 36 ሆስፒታል / ክልል |
| ጤና ጣቢያ | $175,000 | 180 | $ 31,500,000.00 | 180 ጤና ጣቢያ / ክልል |
| ዘይት ፋብሪካ | $25,000,000 | 6 | $ 150,000,000.00 | 2 ዘይት ፋብሪካ / 3 ክልል |
| ሲሚንቶ ፋብሪካ | $45,000,000 | 4 | $ 180,000,000.00 | 1 ሲሚንቶ ፋብሪካ / 3 ክልል |
| **ህዳሴ ግድብ** | **$4,800,000,000** | 1 | **$ 4,800,000,000.00** | |
| እርሻ-እንዱስትሪ ማዕከል- 1 | $230,000,000 | 1 | $ 230,000,000.00 | |
| እርሻ-እንዱስትሪ ማዕከል- 2 | $230,000,000 | 1 | $ 230,000,000.00 | |
| እርሻ-እንዱስትሪ ማዕከል- 3 | $230,000,000 | 1 | $ 230,000,000.00 | |
| እርሻ-እንዱስትሪ ማዕከል- 4 | $230,000,000 | 1 | $ 230,000,000.00 | |
| **ጠቅላላ ድምር** | | | **$8,300,000,000** | |

*ሃያ አመት ሙሉ በህዝብና በአገር አንድነት ላይ ሲያሴርና ሲቀልድ የሰነበተዉ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ባለፉት ሦስት ወራት የህዝብ ወዳጅና የአገር ተቆርቋሪ ለመመስል ሽር ጉድ ማለት ጀምሯል። ካለፈዉ አመት መጨረሻ ጀምሮ ዕድገትና ትራንስፎርሜን ብሎ የጀመረዉን ጣዕመ ቢስ ዘፈኑን አቀንቅኖ ሰይጨርስ የህዳሴዉን ግድብ እንገነባለን እያለ ይህንን ረሃብ፤የዋጋ ንረትና ዘረኝነት ያጎበጠዉን ህዝብ ደምዝህን ስጠኝ እያለ ከዳር ዳር ማተራመስ ጀምሯል። የወያኔ አገዛዝ የኤኮኖሚ አማካሪና የገንዘብ ምንጭ የሆኑት የአለም ባንክና አለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF )የወያኔ አገዛዝ የጀመረዉን የትራንስፎርሜሺን ዕቅድ ሙሉ ለሙሉ ማስጨረስ ቀርቶ ግማሹንም ተግባራዊ ለማድረግ አገሪቱ የገንዘብ አቅም እንደሌላት አስረግጠዉ ተናግረዋል። ይህንን እዉነት ደግሞ ገና ከጥዋቱ አያሌ የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ ጠበብቶች መናገራቸዉ የሚዘነጋ አይደለም። እንግዲህ ይታያችሁ የአምስት አመቱን እቅድ ግማሹን እንኳን የማስፈጸም የገንዘብ አቅም የሌለዉ አገዛዝ ነዉ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንዲሉ ከአገር ዉስጥ በሚገኝ ገንዘብ ብቻ የህዳሴዉን ግድብ እሰራለሁ ብሎ የሚያቅራራዉ። ለመሆኑ ይህ የአገር ቤቱ ገንዘብ ከዬት ነዉ የሚመጣዉ? የህዳሴዉን ግድብ የመሰለ አንድ ሳይሆን ሁለት ወይም ሦስት ግድብ መስራት የሚችል ገንዘብ በወያኔ ሹማምንት ተዘርፎ ባህር ማዶ ባንኮች ዉስጥ ተከምሯል፤ዝርፍያዉ ደግሞ አላቆመም እንደቀጠለ ነዉ ። ታዲያ ይህ አገር ዉስጥ ከእያንዳንዱ ዜጋና ድርጅት ከአገር ዉጭ ደግሞ ከየኤምባሲዉ ሰራተኛና አፍቃሬ ወያኔ ከሆኑ ግለሰቦች ለተጠያቂነት በማያመች መንገድ በነዚሁ ሌቦች የሚሰበሰበዉ ገንዘብ በዶላር ተመንዝሮ ባህር ማዶ ላለመሄዱ ምን ዋስትና አለ?*

| 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 | 1998 | 1999 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 96 | 20.8 | 51.4 | 0 | 75,3 | 62 | 0 | 200.2 | 248.9 |

| 2000 | 2001 | 2002 | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 | 2008 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 94.5 | 565.5 | 332.2 | 96 | **541.2** | **814.8** | **1389.8** | **1306.2** | **2129.5** |

*ዉድ አንባቢ ሆይ እባክህ ተረጋጋ ትንሽ ነዉ የቀረኝ። በዚህ ጽሁፍ መዘረፍህን አይደለም የምነግርህ እሱን አንተም ታዉቀዋለህ። ምን ያህል መዘረፍህንም አይደለም የምነግርህ ፤ ምን ያህል እንደተዘረፍን ቁጥሩ በዉል ሊታወቅ የሚችል አይመስለኝም።በተ. መ. ድ የተረጋገጠዉ 8.4 ቢሊዮን ዶላርም ቢሆን ለግዜዉ በምርመራ የተደረሰበት ነዉ እንጂ የህዳሴዉ ሌቦች የዘረፉንን የገንዘብ መጠንማ እንኳን እኛ የተዘረፍነዉ ዘራፊዎቹም አያዉቁትም። በጽሀፌ ማጠቃለያ ላይ ላሳስብህ የምፈልገዉ ነገር አለኝ ፤ እሱም - የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ካቻምና ፈጣን ዕድገት፤አምና ትራንስፎርሜሺን ዘንድሮ ደግሞ የህዳሴዉ ግድብ እያለ ሲደልለን ከርሟል። እነዚህ ከላይ የምታያቸዉ ሠንጠረዦች የሚያሳዩት ግን የኢትዮጵያን ኤኮኖሚ የዕድገት መጠን ሳይሆን ከኢትዮጵያ ህዝብ ካዝና ዉስጥ በምን ያክል ፍጥነት ብር በዶላር እየተመነዘረ በወያኔ ሹማምንትና ቤተሰቦቻቸዉ ስም ባህር ማዶ ባንኮች ዉስጥ እንደሚከማች ነዉ። ከ2003 -2008 ባሉት ስድስት አመታት ዉስጥ ብቻ የወያኔ መንጋ* ***6.1 ቢሊዮን ዶላር*** *ዘርፎናል። ይህ ደግሞ በአማካይ በአመት* ***1.01 ቢሊዮን ዶላር*** *ወይም ከአገራችን አመታዊ በጀት 35% በላይ ነዉ።*

*ከላይ የተቀመጡትን ሁለት ትናንሽ ሰንጠረዦች በተለይ ቀይ ቀለም ያለበትን ሠንጠረዥ ጠጋ ብሎ የተመለከተ ማንም ሰዉ ሁለት እንግዳ ነገሮች ቁልጭ ብለዉ ይታዩታል። አንደኛዉ ወያኔዎች የኢትዮጵያን ኤኮኖሚ በእጥፍ አሳደግነዉ ብለዉ ቢመፃደቁም ከ2003-2008 ድረስ ባሉት ስድስተ አመታት ዉስጥ በእጥፍ ያደገዉ የነሱ የባህር ማዶ የባንክ ሂሳብ ነዉ እንጂ የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ አይደለም። በሁለተኛ ደረጃ ሠንጠረዡ ላይ የምናየዉ ጉድ ደግሞ ከ2005ቱ (1997) ምርጫ በኋላ ወያኔዎች ሥልጣን እንደጨበጡ ለረጂም ግዜ እንደማይቆዩ ከተረዱ በኋላ የንብረትና ገንዘብ ዘረፋዉን በእጥፍ እንዳሳደጉት ነዉ። ለምሳሌ በ2004 ዓም ወያኔዎች ከአገር ቤት ያሸሹት የህዝብ ገንዘብ **541.2 ሚሊዮን** ዶላር ሲሆን ይህ መጠን በ2008 ወደ **2,129,500,000 ዶላር** አድጓል፤ ይህም በመቶኛ ሲሰላ 393.4% ነዉ።*

*ዉድ አንባቢ - ዛሬ ልልህ የፈለግሁትን ሁሉ ያልኩህ ይመስለኛል ፤ ሆኖም ከመሰናበቴ በፊት አንድ ሆዴ ዉስጥ ዘልቆ ገብቶ ካልወጣሁ እያለ የሚቆረቁረኝ ነገር አለና አዉጥቼዉ ልረፍ። አንተ ይህንን ጽሁፍ የምታነብብ ኢትዮጵያዊ ወገኔ ሆይ ስማኝ - ኃብታችን ተዘርፏል፤መሬታችን ተሸጧል ፤ የዋጋ ንረቱና ረሃቡ እየጨረሰን ነዉ ። ይህ ብቻ አይደለም - መብታችን ተረግጧል፤ነፃነታችን ተቀምቷል፤ሰብዕናችን ተንቋል፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ኢትዮጵያዊነታችን ተዋርዷል። ለመሆኑ ምናችን ነዉ የተረፈዉ? ምንስ እስኪያደርጉን ድረስ ነዉ የምንጠብቀዉ? የምንፈራዉ እንዳይገድሉን ከሆነ በቁም ከገደሉን ቆይቷል። ወገኔ ጉዳያችን "የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም" መሆን አለበት። ካሁን በኋላ እኛ ኢትዮጵያዉያን መፍራት ያለብን "ፍርሃትን" እራሱን ብቻ ነዉ። የፍርሀታችን ግዝፈት የነፃነት፤ የፍትህና የእኩልነት ጥማታችንን ካሳነሰዉ ያለን አማራጭ ተገዝተን በባርነት መኖር ብቻ ነዉ። ይህ ደግሞ የሰዉ ልጆች ምርጫ ሆኖ አያዉቅም ለወደፊትም አይሆንም። ስለዚህ የወያኔን ዝርፊያና ዘረኝነት በአንድ ድምፅ በቃ እንበል። አዎ በቃ!*